የምዕራፍ ሰባት ያክለስ ጥያቄዎች ገፅ 75

- አዛምዱን እና የምርጫ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ፅፋችሁ ስሩ።

ቀሪዎቹን ጥያቄዎች በመግሀፋችሁ ላይ ስሩ።

ምዕራፍ ሰምንት

ራስን መቻል

ራስን የመቻል ጠቀሜታ

✓ ራስን መቻል ማለት በየደረጃው ያለን የራስን ዕውቀት የኢኮኖሚ አቅምና ጉልበት በመጠቀም ኃላፊነትን ወስዶ ለራስ፣ለቤተሰብ እና ለሀገር የሚጠቅሙ ተግባራትን በማከናወን ከጥገኝነት መላቀቅ ማለት ነው።

ራስን የመቻል መገለጫዎች

- በራስ መተማመን
- ራስን መሆን
- የሌሎችን ሀሳብ ማክበር
- ችግር ፈቺ መሆን
- ለላቀ ስራ ክብር መስጠት
- ችሎታን ማወቅ

ጥገኝነት

ጥገኝነት ምንድን ነው?

- ጥገኝነት ማለት የራስ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎት በሌሎች እውቀት፣ገንዘብና ጉልበትና እንዲሟላ መጠበቅ ማለት ነው።

የጥገኝነት መገለጫዎች

- በራስ አለመተማመን
- የራስን ችሎታ አለማወቅ
- ራስን አለመሆን
- የሌሎችን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ መቀበል
- **ማህራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት**

ኮንትሮባንድ

የሀገሪቱን ህግ በመጣስ በህገወጥ መንገድ እቃዎችን ድንበር ጥሶ ከሀገር የማስወጣትና ወደ ሀገር የማስገባት ተግባር ነው። ይህ በሀገር ላይ ማህራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነትን ያስከትላል።

በራስ መተማመን

በራስ የመተማመን ባህሪ የሚገለፅባቸው መንገዶች

- በራስ መተማመን ስሜት ማለት በራስ ላይ እምነት ማሳደር ማለት ነው።
- በራሱ የሚተማን ሰው ሀሳቡን በነፃነት ይገልፃል።
- ከሌሎች የሚሰጡትን ሂሶች ይቀበላል።
- በተለያዩ ጉዳዮዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል።